# ተስፋዬ ገብረአብ፡ ይዘት ከቅርጽ የተጣረሰበት ደራሲ

(ዮሴፍ ወርቁ ደግፌ)

የጋዜጠኛና ደራሲ ተስፋዬ ገብረኣብ ፅሁፋዊ ስራዎች በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ያደረሱትንና የሚያደርሱትን በጎ ያልሆኑ ተፅእኖዎች ለመፃፍ ስነሳ፤ ከልጅነት በሁዋላ ባለው ዘመን (ተስፋዬ ገብረኣብና የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ በልጅነት ዘመን ቢሾፍቱ/ደብረዘይት/ ኖረዋል) ተስፋዬ ገብረኣብ ማነው? የሚል መረጃ በማሰባሰብበት ወቅት ብዙም የማላውቃቸው ዝርዝር መረጃዎችን አገኘሁ፤ ይህም አንደኛው ወገን "ተስፋዬ የማንነት ኪሳራ (Identity Crisis) ውስጥ የገባ፤ ከኢትዮጵያም ከኤርትራም ከሁለቱ ለአንዱም ለመሆን ያልቻለ ምስኪን ሰው ነው" የሚል ሲሆን፤ ይህ ወገን 'ተስፋዬን ተዉት መፅሀፉን እየጻፈና እየሸጠ ይኑር' ባጠቃላይ ተስፋዬ ኖረም አልኖረም ከግል ህይወቱ በስተቀር በማንም ላይ ምንም አይነት ተጽእኖ አያመጣም የሚል አንደምታ ያለው ነው። ሌላኛው ወገን ደግሞ "ተስፋዬ ከወጣትነቱ ጀምሮ የሻቢያ ሰላይ የነበረ የ"ሁለት አለም ሰው" ነው። (ተስፋዬ ባደገበት ደብረዘይት/ቢሾፍቱ/አካባቢ ሻእቢያ ጠንካራ መሰረት ስለነበረው ከወጣትነቱ ጀምሮ ተስፋዬ ሰላይ ነው የሚለው አባባል እውነት ሊሆን ይችላል) ተስፋዬ ገብረአብ በደርግ ዘመን መውደቂያ አካባቢ ለአጭር ጊዜ በውትድርና ሲሰራ ወደ ህወሀት ከድቶ ከሄደ በሁዋላ ደግሞ በጋዜጠኛነት በሰራባቸው ቦታዎችና ጊዜያት ሁሉ የሻእቢያ ሰላይ ነበር፤ ወጣቱ ወታደራዊ ሰላይ ደርግ ሳይነቃበት ነበር ወደ ህወሃት የከዳውና ደርግም ወዲያው የወደቀው፥(ይህንን ተስፋዬ ራሱ በፅሁፎቹ ላይ በከፊል አምኗል) ህወሀት ደግሞ ዘግይቶም ቢሆን ስለላውን ነቅቶበት በቅርቡ ቢያባርረውም፤ ሻእቢያ ግን ተስፋዬ ስለላውን ባለበት ቦታ ሁሉ እንዲቀጥል አድርጎታል" ይላል። ሁለቱም መረጃዎች ኣሳማኝ ቢመስሉም፤ በተለይ ተስፋዬ በአማርኛ ቋንቋ በሚያማልሉ ቃላት ስለሚጽፍ፥ የብዙዎች የዋሆችን ልብ በጽሁፎቹ ስለሚገዛ፥ በኢትዮጵያ ላይ የሚያድርገውን ስለላ ያጠናክርለታል የሚለው ተኣማኒነቱ የጎላ ነው። ለዚህም ማጠናከሪያ የምርጫ 97 ቀውስ አገር አቀፍ አጣሪ ኮሚቴ ም/ሊ/መንበር በነበሩት በዳኛ ወልደ ሚካኤል የቀረበውና የተስፋዬን ሰላይነት የሚያጋልጠው መረጃ ጠንካራ ዋቢ ነው፤ (ይህ መረጃ ከራሱ ከተስፋዬ ምስጢራዊ የእጅ ጽሁፍና የግል ዶክመንት ፎቶ ኮፒ የተደረገ ሲሆን፥ ከተስፋዬ ጋር አብሮት ይኖር ከነበረው ከ'ሰላዩ ሰላይ' ሰው አማካይነት የተገኘ ነው)። ስለዚህ ተስፋዬ ገብረአብ እና "ተስፋዬ ገብረአብ" ሁለት 'የሁለት አለም ሰው'፥ ሰላይም ፀሀፊም ሲሆን፤ ተስፋዬ ለስለላ ስራው መሳካት በተለይ ለኦሮሞ ህዝብ እጅግ

ያዘነና የተቆረቆረ በመምሰል፥ (ኢትዮጵያ፥ ተስፋዬ ዋና አባት ሀገሬ እንደሚላት እንደ ኤርትራ፥ ያለኦሮሞ ህዝብ ህልውና የሚኖራት ይመስል) ፅሁፎቹ እየተጣረሱ ህዝብን የመከፋፈልና የማጋጨት መሰሪ አላማቸውን ያስተላልፋሉ። ውጤቱን በሂደት የምናየው ቢሆንም፤ በዚህ ረገድ ግንዛቤን ማስፋትና ሂደቱንም መከታተል ይገባል።

ወደ ስነ ፅሁፋዊ ስራዎቹ ይዘት ስንመለስ፥ በቅድሚያ የተስፋዬ ገብረአብ መፃህፍት በምሁራዊ የአጻጻፍ ስልት፤ በከባባድ ቃላት (Jargon words) የተጨናነቁ ሳይሆን፥ እንደተረት እና እንደ ጥሩ ወሬ ነጋሪ በቀጥታ የሚፈሱ፥ በተራና በቀላል ቃላት አገላለፅ የተሰደሩ መሆናቸው ግልጽ ነው። ከዚህ የተነሳ ጽሁፎቹ በበርካታ አንባቢዎች ዘንድ እየጣሙ ሳይሰለቹ እንደዋዛ (ጭብጥ ድብቅ አላማቸውን/ መልእክታቸውን/ባለማስተዋል) በስፋት እንዲነበቡ ምክንያት ሆኗል፤ በዚህ በፅሁፎቹ የቅርፅ ሳቢነት ጉዳይ ላይ የሚከራከር ሰው ያለ አይመስለኝም፤ የእኔ ክርክር ያለው ግን በጽሁፎቹ መሰረታዊ ‘ይዘት’ ይህም በጽሁፎቹ ጭብጥ አላማና ተልእኮ አደገኛነት ላይ ነው። ምክንያቱም 'የጽሁፎቹ 'ይዘት' የደራሲዉ የተስፋዬ አላማ ስለሆኑ ነው። አቀራረቤ በጥቅል ግምገማ/እይታ እንጂ፥ በያንዳንዱ የተስፋዬ ጽሁፍ ላይ በመጓዝ አይደለም፥ እንደምሳሌም “የቡርቃ ዝምታ” መጽሀፍን ጥቅል ሀሳብ መውሰድ ብቻ ይበቃል፥••• በ"ስደተኛው ማስታወሻ" መፅሀፍ ላይም ተስፋዬ በሚገባ ቀሽሮ የሚተርክልን የ"ጫልቱ" "ሄለን" በሚለው ስም የመቀየርና "በጫልቱ የአማርኛ አነጋገር ላይም ተቀለደባት" ብሎ የሚነግረን ነገር እጅግ የተጋነነ ከመሆኑም በላይ ይህን ያህል ሚዛን የሚደፋ ችግር አይመስለኝም፥ ምክንያቱም ከተሜ ሁሉ ከገጠር በሚመጡ የኦሮሞ፤ የጉራጌ፥ የአማራ የደቡብ ብሄር ወዘተ ወገኖች የአነጋገር ዘይቤ ላይ እንደቀልድ እየሳቀ ስለሚኖር ነው፥••• ቀላጁ ራሱ ኦሮሞም ጉራጌም አማራም የደቡብ ብሄርም ወዘተ ሆኖ ሳለ፥ ከተሜ በመሆኑ ብቻ (አብዛኛው ከተሜ ህይወቱ ከገጠሩ ህዝብ የማይሻል ቢሆንም) የባላገር ሰዎች የከተሜ የአነጋገር ዘይቤ ስለሌላቸው ብቻ፥ የመቀልድ/የመሳቅ ነገር አለ፥ ነገርግን ትኩረቱ/ቀልዱ በአነጋገር (accent) ላይ እንጂ በማንነት (ዘር) ላይ ፈፅሞ አይደለም። ... በአነጋገር ዘዬ ከመቀልድ ባለፈ ህዝብን በመጥላት እርስበርስ ለማጣላት የሚጽፍን ሰው ምን ለማለት ይቻል ይሆን? ያም ሰው/ፀሀፊ ምናልባት ተስፋዬ ገብረአብ ቢሆንስ? .... ነው'ን'ጂ ... እንዴት?

በፈጠራ ጽሁፍ ውስጥ 'ግነት' የልቦለዱ እንብርት፥ 'ጡዘት' ደግሞ የ'ግነት' ከፍተኛው ደረጃ እንደመሆኑ መጠን፤ በልቦለዱ ውስጥ የግጭቶች በጣም መጋነን (ግነት) ወደ ከፍተኛ ውጥረት (ጡዘት) ይከታል፤ በዚህን ጊዜ የማናውቃቸውና በልቦለድ ውስጥ የተፈጠሩትን እኩይ እና ሰናይ ገጸባህርያት የሚጫወቱትን የፈጠራ ሰዎች በጣም እንድንወዳቸው ወይም ደግሞ በጣም እንድንጠላቸው እንሆናለን። ይህን ስነ ፅሁፋዊ ቴክኒክ በመጠቀም ደራሲ ተስፋዬ ገብረአብ በታሪካዊ ልቦለድ መፅሀፉቹ ውስጥ ግጭቶችን ከሚገባ በላይ በማጋነንና በሀይል በማጦዝ፤ በመፅሀፉ ውስጥ ደራሲው (ተስፋዬ) እንደፈለገ ገዳይና አራጅ አድርጎ በሚስላቸው ገጸ ባህርያት ሰዎች (አማራዎች) እንደፈለገም የሚገደሉና የሚታረዱ አድርጎ በሚስላቸው ገጸባህርያት ሰዎች (ኦሮሞዎች) በመፅሀፉ ላይ ብቻ ሳይሆን፥ በእኛም ኣእምሮ ላይም ተስለው እንዲቀሩ ያደርጋል። ከዚህም የተነሳ የተስፋዬ ያልተገራ ብዕር ዛሬ በእውን ያሉት ኦሮሞዎች አማሮችን እንዲበቀሉዋቸው ቀጥተኛና ግልጽ መልእክት በማስተላለፍ ከፍተኛ ግፊት ያደርጋል። ስለሆነም የተስፋዬ መጽሀፍት በተለይም የኦሮሞን ህዝብ ዳራ አድርጎ የተጻፈው "የቡርቃ ዝምታ" እና ሌሎቹም ለህዝብ ምን መልእክት ነው የሚያስተላልፉት? ፖለቲካዊ አንደምታቸው ምንድነው? አላማቸውና ግባቸውስ? ወዘተ በማለት መመርመር ይገባል። የልብወለድ ፅሁፉ ኣላማና ግብ የሚወሰነው በደራሲው/ጸሀፊው/ ፍላጎት ብቻ በመሆኑ፤ ተስፋዬ ገብረአብ ስነጽሁፍን ጥላቻና ቂም በቀል ለማስፋፋት፥ ለሽብር ስራ፥ ህዝብን እርስበርስ ለማጫረስ ሊጠቀምበት ሞክሯል፤ የኢትዮጵያ ህዝብ ተቻችሎ የመኖር የማስተዋልና የጥበብ ጸጋ ግን ብዙም ሊያንቀሳቅስ ኣልቻለም እንጂ።

ከፖለቲካው በመለስ በሀይማኖት ረገድም ካየነውም "በወንድማማች መካከል ጸብ መዝራት" ከሀጢያቶች ሁሉ እጅግ የከፋ ሀጢያት እንደሆነ መጽሀፍ ቅዱስ ስለሚናገር [ተስፋዬ ክርስቲያን ከሆነ በንስሀ መታደስና፤ የቤተክርስቲያን መሪዎችንም ማነጋገር ያለበት ይመስለኛል] ይህም፥ መጽሀፍ ቅዱስ በመጽሀፈ ምሳሌ ምዕራፍ 6 ቁጥር 16-19 ላይ እግዚኣብሄር የሚጠላቸው ስድስት ነገሮች አሉ፤ ሰባተኛውንም ነፍሱ አጥብቃ ትጸየፈዋለች ይላል፥ እነዚህም፤

1. ትእቢተኛ አይን
2. ሀሰተኛ ምላስ
3. ንፁህ ደም የምታፈስ እጅ

4. ክፉ ሀሳብን የሚያበቅል ልብ

5. ወደ ክፉ የምትሮጥ እግር

6. ሀሰተኛ ምስክር

7. በወንድማማች መካከልም ጠብን የሚዘራ ናቸው።

መጽሐፍ ቅዱስ ሰባተኛውን ሀጢያት ኣስረግጦ የተናገረበት ዋና ምክንያት፥ 6ቱ ሀጢያቶች ባብዛኛው በግል ወይም በአንድ ወይም በጥቂት ሰዎች ላይ የሚፈጸሙ ሃጢያቶች ሲሆኑ፥ 7ኛው በወንድማማች መካከል ጸብን የመዝራት ሀጢያት ግን በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ዕርስበርስ እንዲገዳደሉ በማድረግ በህዝብ (በሀገር) ላይ የሚፈጸም የከፋ ሀጢያት ነው፤ እርስበርስ ግድያው ማቆሚያውም ቀላል ባለመሆኑ ሀጢያቱን የከፋ ያደርገዋል። ከዚህ አንፃር በወንድማማች ህዝብ መካከል ጠብ መዝራት፥ ከሌሎች ሀጢያቶች ይልቅ አደገኛነቱን ለመረዳት ኣያዳግትም።

ደራሲ ተስፋዬ ገብረአብን በግል የመጥላት ችግር ፈፅሞ የለብኝም፥ እጠላውም ዘንድ እምነቴም ሆነ ትውልዴ/አስተዳደጌ/ አይፈቅድልኝም፥••• በስራዎቹ ወይም በጽሁፎቹ ላይ ግን ጥያቄ የመጠየቅ መብት አለኝ፥ ምክንያቱም ህዝብን መሰረት አድርጎ ስለሚጽፍ፥...ከተስፋዬ ጋር በአካል እንደ ጓደኛ ባንተዋወቅም አብሮ አደግ ነን፥ ብንገኛኝ በደንብ የማውቀው ያህል የማነጋግረው ይመስለኛል፤ በአካል ለመገናኘትም ጥረት አድርጌም ነበር አልተመቸኝም እንጂ፤••• እኔም ተስፋዬም ያደግንበት ሀገር (ቢሾፍቱ/ደብረዘይት) ሲሆን፤ የተማርንበት ት/ቤትም ደብረዘይት ኣጠቃላይ ሁ/ደረጃ ት/ቤት ነው፥...እርሱ ከኤርትራ ከመጡ ሰዎች እኔ ደግሞ ከዚያው ከአድዓ/ቢሾፍቱ/ ተወላጆች የተገኘሁ ከመሆናችን በስተቀር፤ ሁለታችንም በተመሳሳይ ማህበራዊ ስነ ልቦና እና ባህል ውስጥ ያደግን ነን። ተስፋዬ በመፅሀፎቹም ስለ ልጅነት ትዝታዎችና ስለደብረዘይት የጠቀሳቸው ስፍራዎች ሁሉ እኔም ያሳለፍኩባቸው ትዝታዎቼ ናቸው፥ ••• እንዲሁም ተስፋዬ 12ኛ ክፍል መቼ እንደጨረሰ በትክክል ኣላውቅም እንጂ (ምናልባት ከእኔ ጋር ሳይጨርስ አይቀርም (?) ከእኔ ጋር የጨረሰ ከሆነ...የተለያየነው እርሱ ከ12ኛ ክፍል በኋላ ወደ ደርግ ወታደርነት ሲገባ (ራሱ በመጽሀፉ እንደገለጸው) እኔ ደግሞ በዚያ ወቅት ግመል በመርፌ ቀዳዳ እንደመሽሎክ ያህል በሚቆጠረው የከፍተኛ ት/ርት ወደ ኮሌጅ/ዩኒቨርስቲ የመግባት እድል በማግኘቴ ነው፤ ... እንዲያ ባይሆን ኖሮ፥ በዚያች የደርግ የመውደቂያ አካባቢ/ወቅት/

ላይም ቢሆን፥ እኔም እንደ ተስፋዬ ወታደርነት ከመቀጠር ያለፈ እድልም አልነበረኝም። እግዚአብሄርም እኛም መድረሻችንን ወሰንንና በዘመነ ኢህአዴግ በተለያዩ የህይወት መንገዶች ላይም ቢሆንም፤ ተስፋዬና እኔ እዚህና እዚያ እየኖርን፤ በአካልም ባይሆን በመፅሀፍቶቹ አማካይነት ለመገናኘት በቃን።

ስለተስፋዬ መጽሀፍት ይህንን ኣስተያየት የምጽፍበት ዋና ምክንያት፤ የተስፋዬ ጽሁፎች በህዝብ ላይ ባላቸው በጎ ያልሆኑ ተጽእኖዎች የተነሳ፥ የሚያመጡትን ከፍተኛ ሀገራዊና ህዝባዊ ጉዳት በመረዳት፥ ለህዝብ ከመቆርቆር አንጻር ነው። ከዚህ በተጨማሪም ተስፋዬ ተሰጥኦውን ባግባቡ በመጠቀም መልካም የሆኑ ትልልቅ የስነጽሁፍ ስራዎችን እንዲያበረክት ለማበረታታት ሲሆን፥ በዚያም ተከብሮ/ተወዶ/ በሰላም እንዲኖር ከመመኘት አንጻር ነው። ከዚህ በመለስ በዋናነት፤ መልካም ያልሆነ ነገር እንዳይከሰት፤ ለሰው ልጆች ሁሉ ምህረትን በማድረግ፥ ፍቅርን በመስጠትና በመቀበል፤ የራስን ሰላምና ደስታ በመጠበቅ፤ የመኖርን ያህል እረፍት የሚሰጥ ነገር የለም በማለት፥ ተስፋዬንም ሆነ ደጋፊዎቹን ለበጎ ስራ አበረታታለሁ። ከሰዎች ጋር በሰላም/በፍቅር/ የመኖር ምስጢር፥ ያለምንም ቅድመሁኔታ ሰዎችን ያለጥላቻ መቀበል ብቻ ሲሆን፥ ይህንንም ለማድረግ እግዚአብሄርን በእውነት ማምለክ ብቻ ነው የሚያስፈልገው። ሰው ሲወለድ በቅድሚያ ሰው ነው፥ የትኛው ሰው? ትግሬ፤ አማራ፤ ኦሮሞ፥ ጉራጌ፥ ጥቁር፥ ነጭ፥ ቢጫ፥ ወዘተ ወይም የሁለትና ሶስት ዘር ቅይጥ፥ ሆኖ ይወለዳል፤ ይህ ማንነትን ከመግለጽ በስተቀር በራሱ ችግር ኣይደለም፥ ሰው ፈልጎ ከዚህና ከዚያ ዘር/ብሄር/ ልወለድ ብሎ አይወለድም። ከዚህ በሁዋላ ደግሞ ሰው በሀገር ደረጃ ኢትዮጵያዊ፥ ኣሜሪካዊ፥ ጃፓናዊ፥ ሶማሊ ወዘተ ይሆናል፥ ይህም ምንም ማለት አይደለም፥ ከማንነት ወደ ዜጋነት (ከአካባቢ ወደ ሀገር) (Nation) መሸጋገር ነው። እንዲሁም ሰው ይህንና ያንን ሀይማኖት መከተሉ አይደለም ችግሩ (ሀይማኖታዊ ተጽእኖ ግምት ውስጥ ሳይገባ) ዋናው የሰው ነገር ያለው ልቡ ላይ ነው፥ ... ሰው ከየትኛውም ዘር ይወለድ በንጹህ ማንነት ካላደገ እና ከኖረ (uncorrupted personality) እንደ ሕጻን ቅን ልብ ስለሌለው፥ የክፋት ሁሉ ምንጭ ይሆናል፥ ለምሳሌ corrupted mind ያላቸው ጥቂት ሰዎች፥ ምንም ሳያጣሩ የዚህ ፅሁፍ ኣቅራቢ ከቀድሞዎቹ ወይም ከአሁኖቹ ገዢ መደቦች ዘውግ/ብሄር ተወላጅ ስለሆነ፥ ለፖለቲካ ፍጆታ ሲል ይህንን ይጽፋል ይላሉ፥ ይህ ግምታቸው ትክክል እንዳልሆነ ለማሳየት ዘሬን መግለጽ ባያስፈልገኝም ኦሮሞ መሆኔን መግለጽ ያለብኝ ይመስለኛል። በሌላ በኩል ደግሞ እንደ ኦሮሞነት በተስፋዬ ገብረአብ ጽሁፎች ለምን እንደማልደሰት የሚሞግቱኝ ኦሮሞዎች ጥቂት አይደሉም፥ ከርእሴ እንዳልወጣ እንጂ እኔ

በኦሮሞነትም በኢትዮጵያዊነትም የማምን ሰው ነኝ፥ እንደ ጃዋር ሞሀመድ የቱ ታስቀድማለህ? ብሎ የሚጠይቅ ካለም መልሴ ኣጭር ነው፥… የሰው ልጅ በሙሉ ከዚህ ወይም ከዚያ ብሄር ወይም ዘር መወለዱ ቀዳሚ ሲሆን፥ የተወለደበትን ሀገር ዜግነት ወይም ደግሞ የወላጆችን ዜግነት መያዝ ደግሞ ቀጥሎ የሚመጣ ነው። …ብሄርና ዜግነት የሚጣረሱ ባይሆንም አንዳንድ ሰዎች ብሄርና ዜግነትን በመቀላቀል የሚጣረስ ይመስላቸዋል፥ ወደ ተነሳሁበት ወደ የተስፋዬ ገብረአብ ጽሁፎች ይዘት ጉዳይ ስመጣ፥ እውነት ነው፥ የተስፋዬ ጽሁፎች ቅርጸ መልካም በመሆናቸው ለማንበብ አይጎረብጡም፥… እኔ የምለው ያለው ግን፥ የተስፋዬ ጽሁፍ ቅርጹ ሳይሆን ይዘቱ አጠያያቂና አነጋጋሪ ብቻ ሳይሆን እጅግ አደገኛ ነው፤••• አደገኛ በመሆኑም ይህንን ጽሁፍ ዘሬን ጠቅሼ ለመፃፍ መነሻ ምክንያት ሆነኝ፤ ዘር መጥቀስ የወቅቱ የፖለቲካ መንፈስ አግንኖት (ከሚገባው በላይ ስለተራገበ) ነው እንጂ፥ ለዘር መቆርቆርና መስራት ድሮም የነበረ፥ ዛሬም በሰለጠኑት ሀገሮች ሳይቀር በጥበብ የሚሰራበት ጉዳይ ነው። ለዘራችን ያለንን ድጋፍ መገለጽ ያለብን በ'የዘሬን ያንዘርዝረኝ' በማለት ሌላውን ዘር በመጥላት ሳይሆን በስራ ብቻ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በአንድነታችን ላይ ትምክህተኝነት (በአንድነት ስም የሌሎችን ማንነት ማፈን) ሲገባባት አገር እንደሚጠፋ ሁሉ፥ በዘር ጉዳይ ላይም ጠባብነት (ጥሩ ኦሮሞ ወይም ጥሩ ትግሬ ለመሆን አማራን መጥላት፥ ወይም እንደሀገር በአንድነት እየኖርን ሳለ፥ ከዘሬ ውጭ ሌላው ዘር የራሱ ጉዳይ ማለት) ሲገባበት፥ ውጤቱ እንደ ትምክህተኝነት ሁሉ ያገር ጥፋት ነው። በመሆኑም ትምክህተኝነት እና ጠባብነት ሁለት የተራራቁ አመለካከቶች ቢሆኑም ውጤታቸው ተመሳሳይ ነው፥ ይህም ኣገር ማጥፋት መሆኑን ብቻ። የጋራ ቤታችንን (ሀገራችንን) ሊያጠፉ የሚችል ነገር ቢኖር ሌላ ጉዳይ ሳይሆን ሁለቱ ጫፎች (ትምክህተኛነትና ጠባብነት) ብቻ ናቸው።

“የተስፋዬ ፅሁፎች ይዘት ችግሩ ምንድነው?” ብለው አንድ የማህበራዊ ሚዲያ ደንበኛ ለጠየቁኝ ጥያቄ እግረመንገዴንም ምላሼን እየሰጠሁ ነው፤… የተስፋዬ ፅሁፎች ይዘት የደራሲው አላማ ነው ባጭሩ፤ ይህም የተስፋዬ ገብረአብ መፅሀፍት አላማ ምንድነው? በአማራና በኦሮሞ ህዝብ መካከል ጸብን በሚዘራ የሚስብ መጽሀፍ ሽያጭ ለመኖር መጣር ነው፡፡ (በዚህ አይነት ስራ የስነ ጽሁፍ ተሸላሚ ሆኖ በ"ሰላም" ለመኖር ይቻል ይሆን?) አይመስለኝም፥ እንዲያውም ይህ አካሄድ ከሙያው የራቀና በህዝብ ላይ ወንጀል መፈጸም ስለሆነ፥ እስከ አለም አቀፍ ፍርድ ቤት (ICC) ድረስ በመጎተት፥ ዘርን ከዘር (ህዝብን ከህዝብ) የማጋጨት/የማጨፋጨፍ/ አንቀጽ ተጥቅሶ በህግ ሊያስጠይቅና ሊያስቀጣ ይችላል።

ለምሳሌ፥ የቀድሞዋ ዩጎዝላቪያንና ሌሎችንም መጥቀስ ይቻላል፥ በአፍሪካም ሌሎቹን ትተን ሩዋንዳን ብንጠቅስ የሁቱና የቱትሲ ሁለት ብሄሮች እርስ በርስ መጨፋጨፍና ወደ አንድ ሚሊዮን የሚጠጋ ህዝብ ማለቅ ምክንያት፥ የፖለቲካ መሪዎች እጅ ብቻ ሳይሆን፤ ጋዜጠኞችና ጸሀፊዎችም በዘር ጥላቻ ተገፋፍተው በህዝብ መካከል ጸብን የመዝራት ፕሮፓጋንዳ በመጻፍና በመቀስቀስ ጭፍጨፋ እንዲደርስ ከፍተኛ ሚና ስለተጫወቱ ነው፥ ይህንን ያደረጉና ያስደረጉ ሁሉ በአለም ላይ ከተሸሸጉበት ቦታ እየተለቀሙ ዛሬ እየታሰሩ ለፍርድ እየቀረቡ ነው። እንግዲህ በህዘቦች መካከል ጥላቻንና በቀልን የመዝራት ጽሁፍ ይዘት የግለሰቦችን ብቻ ሳይሆን የህዝብ እልቂትንም ሊያመጣ ይችላል ማለት ነው፥ ... ስለሆነም ጋዜጠኛ ወይም ጸሀፊ ነኝ የሚል ሁሉ በተለይም የጋዜጠኛነት Ethics/ ስነምግባርን የማያውቅ፤ ወይም ደግሞ እያወቀ ሆንብሎ ህዝብን የማጋጨት ጽሁፍ ቢጽፍ፥ ባጭር ጊዜ ውስጥ ህዝብን በማነሳሳት የማጨራረስ ስራ ሊሰራ ይችላል። ፈጣሪም “በወንድማማች መካከል ጠብ የመዝራት ሀጢያት" ከሀጢያቶች ሁሉ እጅግ የከፋ ሀጢያት አድርጎ ነፍሱ የተጸየፈበት ምክንያትም፥ ይህ ሀጢያት ኣንድን ሰው ብቻ የመግደል ሀጢያት ሳይሆን በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን እርስበርስ ሊያገዳድል የሚችል ሀጢያት ስለሆነ ነው።

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ "ተስፋዬ ገብረአብ ከኦሮሞ በላይ ኦሮሞ ለመሆን የሚጥር ነው" አሉ፥ እኔ ደግሞ የኦሮሞ ህዝብ ብዙሀን (Majority) ሆኖ ሳለ፥ ምናልባትም የዋህነቱን/ቅንነቱን/ በመጠቀም እንደ ህዳጣን (minority) በመቁጠር የበታችነት ስሜት እንዲሰማውና፥ በሌሎች ህዝቦች ላይ የማይገባውን ነገር እንዲያደርግ ተስፋዬ በጽሁፎቹ አማካይነት ቀላል የማይባል የፕሮፓጋንዳ /ቅስቀሳ/ ስራ ማካሄዱ አደገኛ ነውና ይመለስ እላለሁ። የኦሮሞን ህዝብ መሳሪያ ኣድርገው ለመጠቀም ከሚፈልጉት ቡድኖችና ግለሰቦች ውስጥ አንዱ ደራሲና ጋዜጠኛ ተስፋዬ ገብረአብ ነው። ይህ መሰረታዊ ችግርና በሚገባ መታየት ያለበት ጉዳይ ስለሆነ በሌላ ፅሁፍ እመለስበታለሁ። ••• ለዛሬዋ አነስተኛ ጽሁፌ ማጠቃለያ ግን፤ ... ተስፋዬ ከጥላቻ የጸዳ ንጹህ ወጥ ስነፅሁፋዊ ስራ ያስነብበናል ብለን እንጠብቅ በማለት ልሰናበት፥••• ተስፋዬን ለምትደግፉ ወገኖችም ያለእውቀትና ያለአገባብ ደግሞም በግብዝነትና በስሜት አትደግፉት እላለሁ፤ በዚህ ጉዳት እንጂ ጥቅም አይገኝምና፥ ... የምትወዱት ከሆነ ስህተቱን ያለማስመሰል በግልጽ ተናገሩት፤ ••• ተስፋዬን የምትጠሉት ሰዎች ደግሞ ጥላቻችሁን እርሱትና መውደድ ቢያቅታችሁ ያላጥላቻ ተመላለሱ፥••• በንፁህ አእምሮ በእውነት ብቻ ለመተቸት ሞክሩ እንጂ

በተራ ስድብ አይሁን፥ ተራ ስድብ ትርፉ ውርደት ብቻ ነው፤••• ጥላቻም መርዝ ስለሆነ (በሳይንስ የተረጋገጠ) ከናንተ አስወግዱት፥ ቂምና ጥላቻ ጤናን በማቃወስ ተጠይውን ብቻ ሳይሆን ቂመኛውንም/ ጠይውንም ይጎዳልና፥... አለምን በፍቅር እንጂ በጥላቻና በበቀል ማሸነፍም እንደማይቻል ቢያንስ ከኒልሰን ማንዴላና ከማህተማ ጋንዲና ከማርቲን ሉተር ኪንግ ልምድ እንማር፤... በጥላቻ ላይ ተመርኩዞ፥ በጠላትነት ስሜት ተንድርድሮ በጦርነት ማሸነፍ ቢኖርም ጊዜያዊ ነው፤... እናም ሰውን መውደድ ቢያቅት፥ ቢያንስ ሰውን አለመጥላት ይቻላል፥ ይህም ብልህነትና ጥበብም ነው፥••• ስለሆነም ሰውን በየዋህትና በእውነት መንገድ ማቅናት እንጂ የማፍረስ መንገድ መከተል ለማንኛችንም አይበጅም፥... ደራሲ ተስፋዬ የስነ ጽሁፍህ 'ይዘት' እንደ 'ቅርጹ' ያምር ዘንድ ብመኝም፥ ወሳኙ አሁንም አንተ ነህ፥... ነገርግን በ'ቅርጽ' ተስቦ በስሜት ተውጦ በ'ይዘት' ምክንያት መከራ ውስጥ የገባ እጅግ ብዙ ሰው/ህዝብ/ እንዳለ እነግርሀለሁ፥ ጋዜጠኛና ደራሲ ተስፋዬ ገብረአብ የሚበጀውን ማድረግ ይበጃል፥ እምታደንቃቸው እነዚያ ታላላቅ ደራሲዎች/ፀሀፊዎች ስለ ፍቅር፤ ስለ ጥበብ፥ ስለ ፍልስፍና፡ ስለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ፥ ስለ ድህነት፥ ስለ ሙስና፥ ስለ መልካምና ክፉ ስራ፥ ስለ ምህረት እና ይቅርታ፥ ስለ እኩልነት ወዘተ እንጂ አንዳቸውም ህዝብን እርስ በርስ ስለማጫረስ አልጻፉም፥ ••• ታሪካዊ ልቦለድም ከመጻፍ በፊት በሙያው ያሉ አዋቂዎችን ማዋየት መልካም ነው፥ ሊመለስ/ ሊታጠፍ/ ከማይቻል ስህተት ያድናልና፤ ... ሁላችንም ማህበራዊ ሀላፊነት ስላለብን እያንዳንዳችን ለሁላችን የሚበጀውን እናድርግ፥ በስሜት በጉልበት አይሁን፥ ይልቁንም በመቻቻል፤ በመደራደርና በስምምነት፤ በፍቅር፤ በእውቀት፤ በጥበብና በማስተዋል መንገድ እንጂ፥

ፈጣሪ ማስተዋሉን ያድለን